# ከክትባት መርፌዎች በኋላ... ልጅዎ ሕመም ቢሰማው እንደሚያደርጉ

እርስዎንና ልጆችዎን በተላላፊ በሽታ ከመያዝ ለማጠበቅ ስለረዱን እናመሰግናለን፡፡ መርፌዎቹ (ክትባቶቹ) ትንሽ ያሳምሙ ይሆናል፡ በበሽታው መያዝ በጣም የባሰ ነው!

ብዙ ሰዎች ክትባት ካደረጉ በኋላ ማጠነኛ ሕመም ወይም ትኩሳት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የተለመደ ነው፡፡ የእነዚህን ጉዳት የሚያስከትሉ ተቃራኒ ሁኔታዎችን ለመቀነስ የሚረዱ አንዳንድ ሃሳቦች እነሆ፡፡

## የሚያስፈልጉዎት ነገሮች፡

- አንድ <u>የሰውነት ትኩሳት ማለኪያ</u>
- ብዙ <u>ፈሳሽ</u> ለማጠጣት
- ኢቡፕሮፌን ወይም ታይሌኖል (ለልጆችዎና ለእርስዎ የሚስማማው የትኛው እንደሆነ እና የመድኃኒቱ አወሳሰድ እንዴት እንደሆነ ፋርማሲስቱን ጠይቁ)፡፡ **ማናቸውንም ዓይነት አስፒሪን ፈጽሞ ለልጆችዎ እንደማይሰጡ እባክዎ ያስታውሱ፡፡ ለሕፃናትና ለልጆች አደገኛ ነው፡**
- በቀዝቃዛ ውሃ በማነከር በልጅዎ ፊትና ሰውነት ላይ ለማድረግ የሚያገለግል አንድ <u>ንፁሕ ማታጠቢያ ፎጣ</u> ወይም ቁራጭ ጨርቅ

## በልጅዎ ላይ የሚያሚለከቱት ሁኔታ፡

- ልጅዎ ሙቀት ይሰማዋል (እስከ 100.5° ፋ ወይም 38° ሴ)
- ልጅዎ ይቅበጠበጣል
- ልጅዎ ከንፈሩ ይደርቃል

## ምን እንደሚያደርጉ፡

- ለልጅዎ የሚጠጣው ብዙ ፈሳሽ ይስጡ (ውሃ፡ ጌቶሬድ፡ ጭማቂ፡ የጠት ወተት)
- የልጅዎን ልብሶች በከፊል ያወልቁ
- ቀዝቀዝ ባለ (ባማይቀዘቅዝ) ውሃ የተነከረ ንፁሕ ማታጠቢያ ጨርቅ ይጠቀሙ
- ሕመምን ወይም ትኩሳትን ለማስታገስ የሚረዳ አንዳንድ መድኃኒት ለልጅዎ ይስጡ፡ በትክክለኛው ማጠን ማስጠቱን ያረጋግጡ!

## እጅግ ጠቃሚ ምክር፡ የሚከተሉት ከታዩ ለሐኪምዎ ይደውሉ ወይም ወደ ሆስፒታል ይሂዱ፡፡

- ኢቡፕሮፌን ወይም ታይሌኖል ከተሰጠ ከአንድ ሰዓት በኋላ የልጅዎ ትኩሳት ማጠን ከ$100^0$ ፋ ወይም ከ$38^0$ ሴ በላይ ከሆነ፡
- ልጅዎ ከ3 ሰዓት በላይ የሚያስለቅስና ለቅሶውን የሚያቋርጥ ከሆነ፡
- ልጅዎ የሚያስነክሰው፡ የሚያንቀጠቅጠው ወይም የሚያንዘፈዝፈው ከሆነ፡

**Amharic**

After The Shots